ብሰራው ጀነት የምገባበትን ስራ ጠቁሙኝ!' እርሳቸውም እንዲህ አሉት 'በርሱ ላይ አንዳችም ሳታጋራበት አሏህን ማምለክ፣ ግዴታ ሶላትን መስገድ፣ ግዴታ የሆነውን ዘካ መስጠት፣ ረመዷንን መጾም ነው።'

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: "አንድ የገጠር ሰው ወደ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በመምጣት እንዲህ አለ: ' ብሰራው ጀነት የምገባበትን ስራ ጠቁሙኝ!' እርሳቸውም እንዲህ
አሉት 'በርሱ ላይ አንዳችም ሳታጋራበት አሏህን ማምለክ፣ ግዴታ ሶላትን መስገድ፣ ግዴታ የሆነውን ዘካ መስጠት፣ ረመዷንን መጾም
ነው።' እርሱም "ነፍሴ በእጁ በሆነችው እምላለሁ! ከዚህ ምንም አልጨምርም።' ብሎ ዞሮ የሄደ ጊዜ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም
በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ፦ 'ከጀነት ባለቤቶች የሆነን ሰው መመልከት ያስደሰተው ወደዚህ ሰውዬ ይመልከት።' አሉ።"
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

(መኖሪያው) ገጠራማ ስፍራ የሆነ አንድ ሰው ጀነት የሚያስገባውን ስራ እንዲጠቁሙት ወደ ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና መጣ። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጀነት መግባትና ከእሳት መዳን የኢስላም ማእዘናትን በመፈፀም ላይ የተገደበ እንደሆነ መለሱለት። አላህን በብቸኝነት መገዛትና በርሱ ላይ አንዳችንም አለማጋራት፣ በሁሉም ቀንና ምሽቶች አላህ በባሮቹ ላይ ግዴታ ያደረገውን አምስቱን ሶላቶች መስገድ፣ አላህ በአንተ ላይ ግዴታ ያደረገውን የገንዘብ ዘካ ለሚገባው ሰው መስጠት፣ የረመዷን ወርን በወቅቱ በመጾም ላይ መጠባበቅ ናቸው። ሰውዬውም "ነፍሴ በእጁ በሆነችው እምላለሁ! ከእርሶ ከሰማሁት ግዴታ አምልኮዎች አንዳችም ስራ አልጨምርምም አልቀንስምም።" አለ። ዞሮ የሄደ ጊዜም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ: "ከጀነት ባለቤቶች መካከል የሆነን ሰው መመልከት ያስደሰተው ወደዚህ ባላገር (የገጠር) ሰውዬ ይመልከት።"

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/3689